ORIGINAL ARTICLE

The Conversation between Elijah and Mother Earth

***Senkoris Ayalew Kassa*[1] & *Daniel Assefa Kassaye (Ph.D)*[2]**

Abstract

The purpose of this article is to show the literary value of the Ge'ez text of gadla Ǝlǝyas or Elijah the Prophet, focusing on the conversation between the biblical prophet Elijah and Mother Earth. This article presents an English Translation of gadla Ǝlǝyas for the first time. The text presents two characters in debate. In the debate, the two characters Prophet Elijah and mother Earth are symbolised in stylistic icons. The Prophet symbolised as merciless man and the Earth symbolised as kind hearted mother. Why does the text personify the Earth? Are there elements caries the reader can appreciate from the dialogue she carries with the prophet Elijah? Which points are underlined? Why does the Earth criticize this famous prophet? The article showed that the reader is invited to discover the clemency of the Earth before the apparent harshness of the prophet. However, the paper uses a qualitative research with a best text and a critical edition method to address the objective. Despite the researcher has collected five combat of Elijah written in Ge'ez, he chose a manuscript (T) that recorded in fourteenth century for analysis in terms of its grammatical character, readability and precedence. In addition to this research work, this selected text has been translated by the researcher for the first time in this study. This work of translation is also used as a resource and resource for other researchers. Finally, the researcher concludes his thoughts by giving a hint of the ideas that he thinks are good to be studied and used in research.

Keywords: Conversation, Mother Earth and Elijah

አኅጽሮተ ጥናት

የዚህ ጽሑፍ ዐቢይ ጉዳይ በነቢዩ ኤልያስ የገድል ጽሑፍ ውስጥ በግዕዝ ልሳን የተጻፈውን ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ ማሳየት ሲሆን፣ በዋናነት ጥናቱ ያተኮረበት ርእስ ነገርም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፊ ቦታ በተሰጠው በነቢዩ ኤልያስና የእናትነትን ባሕርይ በተዋረሰችው ምድር መካከል በተደረገው ቃለ ምልልስ ላይ ነው። በግዕዙ ጽሑፋም ሁለት ገጸ ባሕርያት በሙግት ወይም በክርክር ሥልት የተቀረጹ ሲሆኑ፣ በዚህ የገጸ ባሕርያት ቅርጽ ደግሞ ነቢዩ ኤልያስና ምድር በባሕርየ ሰብነት ተሥለዋል። በገጸ ባሕርይ የአሣሣል ብልሃትም ነቢዩ ኤልያስ በአቋመ ጠንካራና ሐሳቡን በማይቀይር ሰው መልክ ሲቀረጽ ምድር ደግሞ ርኅራኄ የተሞላው የእናትነትን ባሕርይ ተላብሳ ተወክላለች። እንዲሁም በጥናቱ ውስጥ እንዴት ምድር የሰውን ባሕርይ ተላበሰች? አንባቢስ ከሁለቱ ውይይት ምን ሊረዳ ይችላል? ምድርስ ይሄንን ታዋቂ ነቢይ እንዴት ተቸችው? የአሊጎሪዝም እሳቤስ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር በዚህ ገደል ጽሑፍስ እንዴት ይታያል? የሚሉ ጉዳዮችም በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል፡ ፡ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ከግብ ለማድረስም ጥናቱ የተከተለው የምርምር ዘዴ ዐይነታዊ ሲሆን የገለጻ ሥልትን (description) ደግሞ በማብራሪያነት ተጠቅሟል። በተጨማሪም በግዕዝ የተሰነዱ የነቢዩ ኤልያስ የገድል መጻሕፍት ብዛት አምስት የሚደርሱ ሲሆን አጥኚው ግን የአስራ ዐራተኛውን መቶ ክፍለ ዘመን የገድል ጽሑፍ፣ ከሰዋስዋዊ ባሕርዩና ከተነባቢነቱ እንዲሁም ከቀዳሚነቱ አንጻር ለትንተና መርጦታል። ይህ የተመረጠው ጽሑፍም ከዚህ የምርምር ሥራ በተጨማሪ በዚህ ጥናት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአጥኚው ተተርጉሞ ተዘጋጅቷል። ይህ የትርጉም ሥራም ለሌሎች አጥኚዎች እንደ ግብአትና እንደ ምንጭ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል። በመጨረሻም አጥኚው ቢጠኑና ምርምር ላይ ቢውሉ መልካም ነው ያላቸውን ዐስተያይቶች ሰጥቷል።

ቁልፍ ቃላት፡- ቃለ ምልልስ፣ እናት ምድርና ኤልያስ

1 *PhD Student at Addis Ababa University, department of Linguistics and Philology, Instructor of Geʽez language and literature at the University of Gondar, Ethiopia. Email: senkoris.ayalew@uog.edu.et*

2 *Doctoral thesis advisor, Researcher, instructor at Addis Ababa University in department of Linguistics and Philology, /PhD/ Associate Professor*

This journal is licensed under a creative common Attribution-Noncommercial 4.0. It is accredited to the University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities.
DOI: https://dx.doi.org/10.4314/erjssh.v11i2.6

መግቢያ

ከቀደምት ታላላቅ እስራኤላውያን ነቢያት መካከል አንዱ ነቢዩ ኤልያስ ነው። ነቢዩ ኤልያስ በእስራኤላዊው ንጉሥ አክአብ ዘመነ መንግሥት በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረ ታላቅ ነቢይ ነው (Encyclopedia of religious and spiritual development, 2006:355) ። ይህ ነቢይም እግዚአብሔርን ወክሎ በመቆም ስለአምልኮተ ጣኦት አላስፈላጊነት በአጽንኦት የተናገረና የተለያዩ ተአምራትን ያሳየ ሲሆን ከተአምራቱ ውስጥም፡- ሙት ማስነሣት፣ እሳት ከሰማይ ማውረድና ዝናም እንዳይዘንም ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሰማይን መቆለፉ ይጠቀሳሉ (1ኛ ነገሥት 17.) ። የኤልያስ ቀናኢነትም የተመሠረተው ሙሴ በጻፋቸው ሕጎች ላይ ሲሆን የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔርም በጥብቅ እንዲመለክና በአል የተሰኘው ጣኦትም ከገጸ ምድር እንዲጠፋ በአጽንኦት የተቃወመ ነቢይ ነው (1ኛ ነገሥት 17-21) ። እንደነቢዩ ሄኖክ ቅሉ ሞትን ካልቀመሰ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ውስጥ ከሚጠቀሱት አንዱ ኤልያስ ሲሆን እሱም በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ እንደተነጠቀ የተለያዩ ድርሳናት ያስረዳሉ (2ኛ ነገሥት 2፡11-12)።

ከላይ ከተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ባሻገርም በግዕዝ ተጽፎ በተገኘው የነቢዩ ኤልያስ ገድል ዐዲስ ዕይታን ያካተተ፣ ተጨማሪ መረጃን የሚሰጥ ሥነ ጽሑፋዊ ሀብት ተከሥቷል። ይኸውም ምድር ዋነኛ ተዋናይት ገጸ ባሕርይ ተደርጋና ስለአጠቃላይ ፍጥረት ውክልናን ተሸክማ የተሣለችበት መንገድ ነው። ይሁንም እንጂ ይህንን ውክልና ተሸክማ ከፈጣሪዋ በቀጥታ መልስ ለማግኘት የእናትነትን ሥነ ባሕርይ ተዋርሳ ከነቢዩ ኤልያስ ጋር በጽኑ ትከራከራለች። በክርክሩ ውስጥም የምሕረትንና የፍትኅን መጣረስ በማሳየት፣ የአንባቢን ቀልብ በሚስብ መልኩ የተሰነደ መሆኑ የገድሉን ሥነጽሑፍ ለየት ያደርገዋል። በዚህ ሥነጽሑፍ ውስጥም ለምን የፈጣሪ ምሕረት ከልክ ያለፈ ሆነ? መሐሪ የሆነው ጌታስ ለምን ንጹሓንን ጨምሮ በጋራ ከበደለኞች ጋር እንዲጨነቁ ያደርጋል? ከነዚህ ንጹሓን መካከልስ እንዴት የሰውነት ባሕርይን ያልተላበሰ ፍጥረት በአምሳለ ሰብእ ተከሰተ? የሰው ዘርያ ለሌላቸው ፍጡራን ለምሳሌ፣ እንደዕጽዋት፣ እንስሳት፣ ጅረቶችና ተራሮች ለመሳሰሉት ሁሉ ምድር ጠበቃ ሆና ስትከራከር እሷስ የዚህ ታሪክ ተካፋይ አልነበረችም ወይ ? ወዘተርፈ የሚሉ ሐሳቦች በገድሉ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱ በመሆኑ አጥኚው የግዕዙን ልሳን ወደ አማርኛ በመተርጎም ከላይ የተዘረዘሩ ሥነ ጽሑፋዊ ትንታኔዎችን ለማሳየት ተሞክሯል።

ይሁንም እንጂ ይህ ነቢዩ ኤልያስን በተመለከተ የተከተበው የገድል የግዕዝ ጽሑፍ በየትኛውም የጥናት መስክ ያልተዳሰሰና ያልተተረጎመ እንዲሁም ያልተጠና በመሆኑ ገድሉን በሚመለከት የተሠራ ተዛማጅ ጽሑፍ አልተገኘም። ያም ሆኖ ውስን የሆኑ ስለገድላትና ስለነቢዩ ኤልያስ የተሠሩ ሥራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በኢትዮጵያውያን የጽሕፈት ጥበብ ውስጥ ብዙ ዐይነት ይዘት ያላቸው እንደ ሥነሰብእ፣ ፍልስፍና፣ ነገረ መለኮት፣ ሥነሕዋ፣ ሥነመድኃኒት፣ ታሪክ፣ ገድላት... ወዘተርፈ የተሰነዱ ሲሆን በዋናነት የትርጉም ሥራና ሀገር በቀል ሥራ ተብለው ይከፈላሉ። በዚህ የትርጉም ሥራ ውስጥ ከሚጠቀሱት ሀብቶች መካከልም ገድላት ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። እንደ አምሳሉ (1976፡57) አገላለጽ አንዱ የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ገድል ሲሆን፣ ገድላትም በ13ኛውና በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በብዛት በኢትዮጵያ የተስፋፋበት ዘመን ነው። ከነዚህ ውስጥም ገሚሶች የትርጉም ሥራዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ሀገር በቀል ጽሑፎች እንደነበሩ ያትታሉ።

Michael A. Knibb (1985) ደግሞ ‹The Ethiopic[3] Version of the Lives of the Prophets, II: Isaiah, Jeremiah, Haggai, Zechariah, Malachi, Elijah, Elisha, Nathan, Ahijah, and Joel› በተሰኘ ርእስ የነቢያትን ታሪክ የያዘውን ዜና ነቢያት የተሰኘውን የግዕዝ ጽሑፍ ለመተርጎምና የዕርማት ሥራ ለመሥራት ሞክሯል። በዚህ የጥናት ዳሰሳም የኢሳይያስን፣ የኤርምያስን፣ የሐጌን፣ የሚልክያስን፣ የዘካርያስን፣ የናሆምን፣ የኤልሳዕን የኢዩኤልን፣ የኤልያስን...ታረክ ያካተተውን የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ተመልክቷል። በዚህ ምልከታም የነቢዩ ኤልያስን የትንቢት ዘመንና የልደት ሁኔታውን እንዲሁም የነበረበት ዘመንም በመጽሐፍ ቅዱስ ባይጠቀስም በ8ኛው ምዕተ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንደነበር ተገልጿል። ይህ Michael A. Knibb የተሰኘ ተመራማሪም የግዕዙን ብራና ፎቶ እያነሣ እንደ ማስረጃ በእየገጹ አስደግፎታል። ለምሳሌ ኤልያስን በሚመለከት እንደማሳያ ከወሰደው የብራና ገጽ አንዱ ይህ ሲሆን፣ የትርጉም ሥራውንም ወደ እንግሊዝኛ ቀይሮታል። ይሁንም እንጂ ከገድሉ ጋር የሚገናኝ ሥራ አይደለም። ምናልባትም

3 *The word 'Ethiopic' does not refer the country- Ethiopia but, it is indicating the language of Ethiopia the so called Ge'ez. Some indigenous readers comment the word to be changed into Ge'ez but Ethiopic is not strange for academic world.*

ለዚህ *ሥራ* ቅርበት እንዲኖረው ያደረገው ስለነቢዩ ኤልያስ *መናገሩ* ብቻ ነው።

ሌላው Steven Kaplan (2012) የተሰኘ ምሁር የሠራው ጥናታዊ ጽሑፍ ተጠቃሽ ነው። ይህ ጥናትም ገድላትንና የኢትዮጵያ የመካከለኛውን ዘመን ታሪክ የሚመለከት ሲሆን የም*ሥራ*ቃውያን ክርስትና፣ ባህልና ቋንቋ ከመካከለኛው የኢትዮጵያ ባህል ጋር ያለውን ተዛምዶና ትስስር የሚያትት *ሥራ* ነው። ይህም *ሥራ* ከገድለ ኤልያስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለውም፤ ይልቁንም ስለገድላት ማውራቱ እንጂ።



በሁለተኛ ደረጃ፣ Steven Kaplan (1982) የሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የሠራው የመመረቂያ ጽሑፍ ሁለተኛው ተጠቃሽ ነው። ይህ የገዳሙ ቅዱስ ሰውና የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊነት (The Monastic Holy man and the Christianization of Ethiopia 1270-1468) ተብሎ ርእስ የተሰጠው ጥናት በሔብሩ ዩኒቨርሲቲ ከ1270-1468 ዓመተ ምሕረት ያለውን የገድላት ሁኔታ የመረመረ ሲሆን ስለ ገድል ምንነትና የት መጣሹንም ከገሪክ እንደሆነ ሳያሰፍር አላለፈም። ይህ አጥኚም ከላይ እንደ ተጠቀሱት ግለሰብ ገድላት በሁለት ጎራ እንደሚገኙና አካባቢያዊ *ሥራ* እንዲሁም የትርጉም *ሥራ* ተብለው እንደሚከፈሉ አስረድቷል። ለማሳያ የሚሆንም እንደ ምሳሌ ገድለ ሰማዕታትን በዋቢነት ደጋግሞ ጠቅሷል። በአክሱም ዘመን ውሱን የትርጉም *ሥራ*ዎች ቢሰነዱም በአብዛኛው ግን ግዙፍ የሥነ ጽሑፍ ዘውግ የተመዘገበለት ገድላት ግን በዋናነት ተጠቃሽ ነው።

ሌላው ሀገር በቀል *ሥራ*፣Taddesse (1970) ስለገድል የሠሩት *ሥራ* ነው። ይህ *ሥራ* (Hagiographies and the Reconstruction of Medieval Ethiopian History) በተባለ ርእስ ጉዳይ የተቀነበበ ሲሆን የኢትዮጵያን የመካከለኛውን ዘመን ታሪክ ለማጥናት ገድላት፣ ድርሳናትና ዜና መዋዕላት ጉልህ ሚና እንደሚጫወቱ በጥናቱ ተረጋግጧል። በእርግጥ ይህ ጥናትም ቢሆን ስለ ገድላትና ድርሳናት ማውራቱ እንጂ ከገድለ ኤልያስ ጋር በይዘት ደረጃ ግንኙነት የለውም። ይሁንም እንጂ የግዕዝ ድርሳናትና ገድላት ከሚባሉት ውስጥ ግን ገድለ ኤልያስ ነቢይ አንድ ኢትዮጵያዊ የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ነው።

ሌላኛው ሰለገድለ ተክለ ሃይማኖት የሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ትንታኔ የሠሩት Tesfaye (1997) የተባሉት ምሁር ናቸው። እኒህ ተመራማሪም (A Structural Analysis of Gädlä Täklä Haymanot) በተሰኘ ርእስ ነገር ጥናት ያካሔዱ ሲሆን በዋናነትም የተክለሃይማኖትን ገድል ከቅርጽ አንጻር ምን ዐይነት ይዘታዊ *መሥመር* እንዳለውና ከታሪክ እስከተአምር ከገድል እስከቃልኪዳን ያለውን ፍሰት የሚዳስስ ነው። በተጨማሪም ሊቁ ኪዳነ ወልድ ክፍሌንና ሌሎቹን የውጭ ጸሐፊዎች በማጣቀስም ስለ ገድል ምንነትና የትርጉም ጥንተ አመጣቱን በሚገባ አስረድተዋል። ይሁንም እንጂ ከገድል አንጻር ሲታይ ካልሆነ በቀር ከነቢዩ ኤልያስ ጋር ተዛምዶ የለውም።

በተጨማሪም ዘውዴ (Zewdie 2023) በፈረንጆች አቆጣጠር ስለገድለ ፍቅርተ ክርስቶስ የሠሩት *ሥራ* ተጠቃሽ ነው፡፡ በዋናነትም የቅዱሳት ሴቶች ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋን በገድል ውስጥ የሚያሳይ ሲሆን በጥናታቸው (Textual Value of an Ethiopic Woman Hagiography: Gädlä St. F q rtä Kr stos) በተሰኘ የጥናት ርእስ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተሠራ ጥናት ነው። ይህም ጥናት ከገድለ ኤልያስ ጋር በቀጥታ ባይገናኝም በግዕዝ መጻፉና ገድል የሚለውን ስያሜ መያዙ ግን ያገ*ራ*ብታቸዋል።

ከዚህ ባሻገር ርእስ ነገሩ የገድል ጉዳይ አይሁን እንጂ ከነቢዩ ኤልያስ ጋር ግን በቀጥታ የሚገናኙ ውስን *ሥራ*ዎችን አጥኚው ለመዳሰስ ሞክሯል። በእርግጥ አብዛኞቹ *ሥራ*ዎች ከብሉይ ኪዳን በተለይም ከመጽሐፈ ነገሥት ጋር የተገናኘ ቢሆንም ቅሉ እንደሚከተለው ለማስፈር ተሞክሯል። በአንድ የጥናት መድበል ውስጥ ከሚካተቱ *ሥራ*ዎች (From the treasure house of

mysteries) ከተሰኘው መድበል ውስጥ በሴርያክ ቋንቋ ተጽፎና ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ የምናገኘው ሥራ አንዱ ከነቢዩ ኤልያስ ታሪክ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው። እንዲያውም ይህ ጽሑፍ ከገድሉ ታሪክ ጋርም በጥብቅ የሚዛመድ ነው። ይህ በ(Saint Vladimir's Seminary, 2012:117) ውስጥ የታተመው መድበል፣ የምድርን የሰውነት ባሕርይ መላበሰን እንደገድሉ እረጅም ትረካን አካትቶ ባይገኝም በተወሰነ ክፍል ግን ምድር አፍ አውጥታ ስትናገርና ውሃውንም ከፊቱ ላይ ስትውጠው የሚነገር ክፍል አለ። ይህም ሐሳብ ከሌሎቹ ጽሑፎች ይልቅ ከገድሉ ጋር ግንኙነት ያለው ሥራ መሆኑን መገንዘብ ያስችላል።

ሌላው David Frankfurter (1994) የሠሩት ሥራ ነው። ይኽ ሥራ በኮፕቲክ ልሳን የተጻፈውን የኤልያስን ራእይ (Coptic Apocalypse of Elijah) ምንጭ በማድረግ የተሠራ ሲሆን፣ በአብዛኛው በመጽሐፈ ነገሥት የሠፈረውን ታሪክ የሚያትትና ኤልያስ በአክአብ ኤልዛቤል ዘመነ መንግሥት ጊዜ ያሳለፈውን ውጣ ውረድና የኤልያስን የትንቢቱን ኀያልነትም የሚያሳይ ነው። በእርግጥ በሐሳብ ደረጃም በውስን ገጽታዎች ከነቢዩ ኤልያስ የግዕዙ የገድል ጽሑፍ ጋር የሚገናኝ ቢሆንም ቅሉ የራእዩ ሥራ በኮፕቲክ ቋንቋ ሲሆን የገድሉ ሥራ ደግሞ የተከተበው በግዕዝ ቋንቋ ነው። ይህ የጥንታውያን የግብጾች ልሳን ብዙ ሃይማኖታዊ ሥራዎችን ሰንዶ የያዘ ቢሆንም የአፍ መፍቻና የመነጋገሪያ ቋንቋው ግን ከብዙ ዘመን በኋላ አረብኛ ሆኗል፡ ፡ ይህ የ David Frankfurter ሥራም ከቆስጠንጢኖስ በፊት በግብጽ ያሉት ቅዱሳን ሰማዕታት የአምልኮ ሥራቸው ምን ዐይነት ገጽታ እንደነበረው የሚያትት ሆኖ ጽሑፉም (The Cult of the Martyrs in Egypt before Constantine: The Evidence of the Coptic Apocalypse of Elijah) በሚል ርእስ የተዘጋጀ ነው። ሌላውና የመጨረሻው በ Vlad Bedros (2022) የተዘጋጀው አርቲክል የነበዩ ኤልያስን ገዳማዊ ሕይወት የሚያሳይ የሥዕላት ስብስብ ሥራ ላይ የሚያተኩር ነው። ይህ የትንተና ሥራም የኤልያስን ምንነትና የቀናኢነቱን ጥግ የሚያሳይ ነው። ይህ ርእስ ነገርም "The Prophet Elijah in Moldavian Iconography, ca. 1480-1530: Liturgical and Devotional Contexts" በሚል ርእስ ተሰንዷል።

ይሁንም እንጂ ከላይ የተጠቀሱት ሥራዎች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ከገድሉ ወይም ከነቢዩ ኤልያስ ጋር የተገናኙ ቢሆኑም ቅሉ፣ ይህ የነቢዩ ኤልያስ ገድል ግን ምንም ዐይነት ጥናት ያልተካሄደበትና ሥነ ጽሑፋዊ ዘውጉም ከሌሎች ገድላት የተለየ በመሆኑ ለጥናት ተመርጧል።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ሚናም የነቢዩ ኢልያስን የገድል ጽሑፍ በመመርመር ሥነ ጽሑፋዊ ዘውጉን ማሳየትና ምድር ከነቢዩ ኤልያስ ጋር የምታደርገውን ጠንካራ ቃለ ምልልስ ማሳየት ነው። ጠቀሜታውም ያልታየውንና ያልተጠናውን የግዕዝን የሥነ ጽሑፍ ሀብት ለተመራማሪና ለአንባቢ እንዲሁም ለምርምር ተቋማት ተደራሽ ማድረግ ነው።

ይህ የግዕዝ ገድል ጽሑፍ እንዲጠና ካነሣሡ ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው የተጻፈለት ነቢይና የጽሑፉ ይዘት አስገራሚነት ነው። ገድል የሚለው ሐሳብ ከተጋደሉ፣ ስለ ፈጣሪያቸው መስክረው ከተሠቃዩና ከሞቱ እንዲሁም ሰማዕትነትን ከተቀበሉ በኋላ የሚመጣ ሃይማኖታዊ ጽሑፍ ሲሆን ይህ የገድል ጽሑፍ ግን ለዓለም ሊተዋወቅ የሚገባ ልዩ ገጽታን የያዘ ጽሑፍ ነው። ምክንያቱም ነቢዩ ኤልያስ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በእሳት ሠረገላ ተነጥቆ ብሔረ ሕያዋን መኖሩንና በዳግም ምጽአትም ተመልሶ በምድር ላይ እንደሚከሠት ይነግረናል (Mark 9:13)። ስለሆነም ነቢዩ ኤልያስ በሠይፍ እንደሰማዕታት አልተቀላም፤ በእሳት አልተቃጠለም፤ በአራዊት አልተነከሰም፤ እንዲሁም ሞትን አልቀመሰም። ነገር ግን እንደተሰቀሉት፣ አንገታቸውን እንደተቀሉ፣ ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ እንደተለዩ ጻድቃንና ሰማዕታት ሁሉ በሕይወት ላለው ለነቢዩ ኤልያስም የገድል መጽሐፍ መከተቡ ግርምትን የሚፈጥርና ዐዲስ የሥነ ጽሑፍ ዘውግን የሚያስተዋውቅ መሆኑ ነው። ይህ ሐሳብ በሌሎች የክርስትና ተቋማት ውስጥም የገድል እሳቤ ሞተ ሥጋን የሚያመለክት ሲሆን የኢትዮጵያውያን[4] የገደል የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ግን ሞትን ብቻ ሳይሆን ውጣ ውረድ ያለበትን ዓለም ሁሉ ገድል ብለው ሊሰይሙት እንደሚችሉ የሚያመላክት ጥናት ነው። ለምሳሌ ደራሲው የመጀመሪያ ጽሑፉን ሲከፈት፤ < <በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ንጽሕፍ ገድሎ ለኤልያስ ነቢይ> > ይላል። ትርጉሙም አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በእግዚአብሔር ረዳትነት የነቢዩ ኤልያስን ገድል ለመጽሐፍ እንጀምራለን የሚል ነው። ስለሆነም ገድል ምንድን ነው? ለሚለው ሐሳብ ተጨመሪ ማብራሪያ ያስፈልጋል እንጂ ሞትን ብቻ አለማመልከቱን የሚያሳይ ነው (Tesfaye Gebre Mariam 1997)።

4 ነቢዩ ኤልያስ በእስራኤል ሀገር የተወለደ ቢሆንም ቅሉ ገድሉ ተጽፎ የሚገኘ ግን በግዕዝ ቋንቋ ነው፣ ይኽ ማለትም ኢትዮጵያውያን የግላቸው የሆነ የገድል አጻጻፍ ዘውግ ነበራቸው እንድንል የሚያደርግ ነው፣ በእርግጥ በብዛት የተለመደውን የገድል ቅርጽ ያላካተተ ቢሆንም፡፡

የአጠናን ዘዴ

ይህ የጥናት ዘዴ የሚከተለው የማጥኛ ሥልት ዐይነታዊ ምርምርን ሲሆን ሥነ ጽሑፋዊ ማሳያውም ገለጻ ሥልት[5] ነው። የሚጠናው መረጃም ጥንታዊ የግዕዝ ጽሑፍ የሆነው የነቢዩ ኤልያስ ገድል ሲሆን፣ ገድሉም አምስት ዐይነት ቅጅዎች ተገኝተውለታል። እንዚህን ቅጅዎችም አጥኚው ለእያንዳንዳቸው ማብራሪያና ትንታኔ አይሰጥም። ይልቁንም አንዱንና ጥንታዊ የሆነውን ብራና ወይም የአስራ ዐራተኛውን መቶ ክፍለ ዘመን የጥጎር ማርያምን የብራና ጽሑፍ በመምረጥ ለመተርጎምና ለመተንተን ተመርጧል። ይህ ብራና የተመረጠበት መንገድም ለሌሎች ብራናዎች መሠረት ወይም ቀደምት መሆኑን በመገንዘብ ሲሆን የሰዋስዋዊ መንገዱና ተነባቢነቱም ከሌሎች የተሻለ በመሆኑ ነው። ሌሎች ዐራቱ ብራናዎችም አንዳንድ ጊዜ ለሚከሰቱ ውዝግቦች በምስክርነት እየመጡ ለማረሚያና ለማስተካከያነት አገልግለዋል።

ይህ የጥጎር ማርያም የብራና መዝገብም ጥቅል መጠሪያ ስሙ ገድለ ሰማዕታት የሚባል ሲሆን ብዙ የቅዱሳን ታሪክም በአንድ መድበል ውስጥ ተካትተውበታል። ከእነዚህ ታሪኮች መካከል የነቢዩ ኤልያስ ገድል እራሱን የቻለ አንድ ምዕራፍ ሆኖ ይገኛል። ይኸንን ገድልም አጥኚው ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ በመተርጎም ጥልቅ እርማት እየሠራበት ሲሆን የነቢዩ ኤልያስንና የምድርን ክርክር ያሳዩልኛል ያላቸውን አንቀጾች ደግሞ ከሙሉ ጽሑፉ ቆርጦ በማውጣትና በመተርጎም ወደ አማርኛ ተርጉሟቸዋል።

የተሰበሰቡ መረጃዎች ከታች በሰንጠረዥ የሰፈሩት ብራናዎች ሲሆኑ ከመካከላቸው ተመርጦ የተተረጎመው ደግሞ በመለያ ቁጥር (EMML 6903) የሚገኘው የጥጎር ማርያም[6] ገድለ ሰማዕታት የተባለው የብራና መጽሐፍ ነው። ሌሎቹ ዐራቱ ደግሞ የዳጋ እስጢፋኖስ፣ የገዳመ አስቄጥስ፣ የወሎ አባ ውባለ የግልና በቤተ ክህነት ቤተ መጻሕፍት የሚገኘው ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት በቅርብ ያጻፉት ነው። በእርግጥ በቤተ ክህነት ቤተ መጻሕፍት ከሚገኘው ብራና ውጭ ሁሉም ካታሎግ ተሠርቶላቸው ቅጃቸው በውጭ ሀገር ተቋማት የሚገኙ ናቸው። ሌላው አንዱ ከፈረንሳይ ላይብራሪ የሚገኘው የኤልያስ ገድል ግን በሀገር ውስጥ ገዳማት ወይም ገድሉ ይገኝበታል ተብሎ በሚታሰበው ቦታ አልተገኘም። ምናልባትም የደብረ ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ሀብት ሊሆን እንደሚችል ቢገመትም ከቦታው ግን ይህ ብራና የለም። ነገር ግን በፈረንሳይ ላይብራሪ (Bnf 133) በሚል መለያ ቁጥር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

Name of the Mss . (ስም)	**Project No.** (ተ . ቁ)	**Age of the Mss .** (ዓ . ም)
EMML	2796	15th century.
EMML	6903	14th century.
Gallica/ Bnf.	133	15th century.
EMIP	MM00226	15th century.
Gädlä Sämaətat	Without project number	20th century.

በእርግጥ አንዳንድ የግሪክ፣ የሴሪያክና የኮፕቲክ ድርሳና[7] ት በትንሹም ቢሆን ተዛምዶ ቢኖራቸውም የዚህ ገድል፣ ኤልያስ ከምድር ጋር የሚያደርገው ንግግር ግን በተለየ መልኩ መሆኑ ለጥናት ጋብዞታል። በአብዛኛው ግዑዛን አካላት የሚባሉት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ሲናገሩ ወይም ሲደነቁ እንመለከታለን። ይሁንም እንጂ አጭርና ምጥን የሆነ ነው። በነቢዩ የኤልያስ ገድል ግን የምንመለከተው ከተለመደው በተለየ ረጅም ንግግርና ክርክር እንዲሁም ጥላቻን የሚያሳይ ነው። ይህም ገድሉን በዐዲስ የጽሒፈት

5 *ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተው ተመራማሪው አንድ ጉዳይ አንሥቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ሁኔታ መሠረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርበበት ነው (ያለው፣ 1998፡20)፡፡*

6 *በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የምትገኝ ቀበሌ ስትሆን ከአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት ወይም በዘመነ ዘርዐ ያዕቆብ እንደተመሠረተችም በትውፊት የሚነገርላት ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡*

7 Francesca Prome Teabarone (2008:1) in the University of Palermo, writes his theological article from pieces of Greek Homilies an elegant work entitled “The Image of Prophet Elijah in PS. Chrysostom the Greek Homilies” The general concept of the paper is concerning the life style of prophet Elijah with the Bible and the Homilies.

ዘውግ እንዲታይ ያደርገዋል።

በመሆኑም አጥኚው የጥንር ማርያምን ብራና በመምረጥና ወደ አማርኛው ትርጉም በመመለስ እንደሚከተለው ጽሑፋዊ ትንታኔ ለመስጠት ሞክሯል። ከግዕዙ አንቀጽ ቀጥሎም ከብራናው የተወሰደበትን ገጽና ዐምድ ጭምር በምንጭነት ለማስፈር ሞክሯል። የትርጉም ሥራውም በአጥኚው የተከናወነና የመጀመሪያ ሥራ ሲሆን ትርጉሙም የቃል በቃል ትርጉም ብቻ ሳይሆን ሐሳብንም በመውሰድ ሥነ ጽሑፋዊ ውበቱን ጠብቆ ለአንባቢ ግልጽ እንዲሆን ተደርጎ የተተረጎመ ነው።

የገድለ ኤልያስ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ አንቀጾችና የአማርኛው ትርጉም ከትንታኔ ጋር

የነቢዩ ኤልያስ መንፈሳዊ ዐቅም

በእርግጥ ኤልያስ በፈጣሪው ስም ፍጹም የሆነ መሐላ ምሎ በመነሣቱ ምክንያት ከሰማይ በታች ላለው ነገር ሁሉ ሙሉ ኀይል[8] ተሰጥቶት እንደ ነበር በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 17- 21 ሰፍሯል። ጠቅላላ ሐሳቡም እግዚአብሔር የዘጋውን ማን ይከፍታል፤ እግዚአብሔር የከፈተውንስ ማን ይዘጋል ዐይነት ነው። በእርግጥ የነቢያት ሥልጣን ጠንካራና ቃላቸውም በተናገሩት መልኩ የሚፈጸም ቢሆንም ቅሉ ነቢዩ ኤልያስን ግን ለየት የሚያደርገው ቀናኢነቱና ስለፈጣሪው የሚወስነው ከባድ ቅጣት ነው። ይህ ቅጣትም ለምድርና በእሷ ላይ ለሚኖሩት ሁሉ ፈተና ሆኖባቸው እንመለከታለን። በመሆኑም የነቢዩ ኤልያስን የንዴት ጣሪያና የምድርንም የጭንቀት መንሥኤ ቀጣዩ አንቀጽ ለማሳየት ይሞክራል።

ገድለ ኤልያስ ነቢይ

ግዕዝ፡-......... (ዘአያኩ፡ ማዕዖ፡ ወመኑ፡ ይክል፡ አርኅዎ። ወያእምሩ፡ ነገሥት፡ ምድር እስመ፡ ኀያል፡ ውእቱ፡ አምላከ፡ ኤልያስ፡ ነቢይ፡ ውእቱ፡ ፈጣሬ፡ ሰማይ፡ ወምድር። ለእለ፡ የአምኑ፡ ቦቱ፡ የሐይዎሙ፡ ወያወርሶሙ፡ መንግሥቶ። ወጸርሐ፡ በዐቢይ፡ ቃል፡ ገብረ፡ እግዚ አብሔር፡ ኤልያስ፡ ነቢይ) (EMML-6903 T159vb- T159ra [9])።

አማርኛ፡.... እኔ የዘጋሁት[10] ን በር (መዝጊያ) ማን ሊከፍተው ይችላል የምድርና የሰማይ ፈጣሪ የሆነው እንዲሁም የነቢዩ ኤልያስ አምላክ ብርቱ እንደሆነም የምድር ነገሥታት ይወቁት። በእርሱም የሚያምኑበትን ያድናቸዋል። መንግሥቱንም ያወርሳቸዋል> >። የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነው ነቢዩ ኤልያስም በታላቅ ድምጽ እንዲህ ሲል አሰምቶ ተናገረ።

በእርግጥ በግዕዙ ላይ የምንመለከተው <ጸርሐ[11] > የሚለወን ቃል እንዲሁ በጥሬው ከተረጎምነው <ጮኸ> የሚል ነጠላ ትርጉም

8 “We suggest a threefold reason as to the secret of Elijah’s strength First his praying. “Elijah was a man subject to like passions as we are, and he prayed earnestly that it might not rain, and it rained not on the earth by the space of three years and six months” (Jam 5:17). Let it be duly noted that the Prophet did not begin his fervent supplications after his appearance before Ahab, but six months before! Here, then, lies the explanation of his assurance and boldness before the king. Prayer in private was the source of his power in public: he could stand unabashed in the presence of the wicked monarch because he had knelt in humility before God. But let it also be carefully observed that the Prophet had “prayed earnestly”: no formal and spiritless devotion was his that accomplished nothing, but whole-hearted, fervent and effectual.” On the Book of the Life of Elijah, (A.W. Pink 1997:8)

9 ‘T’- Indicates that the place of the manuscript, Tigor Mariam. ‘V’ is referring Verso or the left side of the parchment and ‘R’ the right side of the parchment or the page. And small ‘a’ and small ‘b’ are indicators of the manuscript columns. The Geez manuscripts sometimes could be written in one column, in two columns, in three columns and four columns and more. These symbols are international Philological terms.

10 This paragraph indicates that the climax of Elijah’s narking.

11 “ርእየ ኢሳኢያስ ነቢይ በመንፈሰ ትንቢት ምሥጢሮ ለአማኑኤል ወበእንተዝ ጸርሐ እንዘ ይብል ሕፃን ተወልደ ለነ ወልድ ተውህበ ለነ” ጸርሐ የሚለውን ቃል በአንድምታው ቦታ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሲተረጉሙት- አሰምቶ ተናገረ ሲል ነው በማለት ይተረጉሙታል፡፡ (ትንቢተ ኢሳ. እና የሰኞ ውዳሴ ማርያም) “ማርያም ድንግል ትጸርሕ በቤተ መቅደስ ወትብል የአምር እግዚአብሔር”...(የአርብ ውዳሴ ማርያም) የሚለውንመ አሰምታ ተናገረች ሲል ነው ብለው ተርጉመውታል፡፡ ኤልያስም እንዲሁ፡፡

ሊሰጥ ይችላል እንጂስ አሰምቶ መናገርን የሚጠቁም ነው። በዚህ አንቀጽ ውስጥ የምንመለከተው በእግዚአብሔርና በነቢዩ ኤልያስ መከከል የሚታየውን የቃል ኪዳን ሰነድ ነው። ለምሳሌ በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 17፥ 1 ጀምሮ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤልያስ መጣ የሚለውን ማጤን ተገቢ ነው። ይህንን መመኪያም ኤልያስ ስላገኘ በድፍረት ተናገረ፤ ማንም እኔ የዘጋሁትን ሊከፍት አይችልም አለ፤ ይህ ለብቻው ያደረገው ሳይሆን አምላኩን በመተማመን ነው።

ይህ ከላይ የተገለጸው አንቀጽም እንግዲህ ከምድር ጋር ላለው እሰጣ አገባ እንደ ሰበበ ግጭት መንሥኤ ስለሆነ በትንሹም ቢሆን ለማሳያ ቀርቧል።

የምድር ጭንቀት

ንጉሥ አክአብ[12] ና ቤተሰቡ ጣኦት በማምለካቸው የተነሣ ነቢዩ ኤልያስ ከመጠን በላይ ተናደደ። እርሱም ሰማይ ለምድር ዝናም እንዳይሰጣት አዘዘ (1ኛ ነገሥት 17)። ከዚህ የተነሣም ምድር መጨነቅ ጀመረች። ነገር ግን፣ ነቢዩ ኤልያስ ይህንን መልእክት ለማን ነበር የሚናገረው? ታዳሚውስ ማን ነበር? ምናልባትም መልእክቱ ሰዎችን ለማስፈራራት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በሚደንቅና ሥነ ጽሑፋዊ ውበት በተሞላው ቃል ምድር ለኤልያስ ምላሽ ስትሰጥ የሚያሳይ ጠንከር ያለ ቃል ምልልስ መኖሩ ነው። ምናልባት ምድር የእግዚአብሔርን ቸርነት ለማሳየት በአምሳለ ሰብእ እናትነትን ወክላ ቀርባ ይሆንን? በዚህ የገድል ጽሑፍ ውስጥ ምድር በሁለት ነገሮች ሰውኛ ባሕርይን ተላብሳ እንመለከታታለን። አንድኛ በፍርሃት ተውጣ እናያታለን፤ ሁለተኛ ስትንቀጠቀጥ ወይም ስትርድ እንመለከታታለን። ከዚህ ጭንቀት በኋላም ምድር በፍርሃት ችግሯን ለኤልያስ ስታቀርብ ትታያለች። ከኤልያስ በሰማችው ነገርም በጣም ከፍቷትና አዝና ችግሯን ትናገራለች። የሚደርስባትን መከራም ታስታውሳለች። በፍጥረቱ ሁሉ የሰውን ልጅ ጨምሮ ለሚደርስባት መከራ ሁሉ ስትጨነቅ ጽሑፉ ያሳያል። በእርግጥ ምድርም ከሌሎች ፍጡራን ጋር ያላትን ግንኙነት ወይም ተለይታ ከአደጋው የማትተርፍ መሆኗን ተረድታለች። በሌላ አባባል የሌሎች ፍጡራን ጭንቀት፣ ወይም በእርሷ ላይ የሚኖሩ የተለያዩ ፍጥረታት ችግር ለእርሷ ጭምር እንደሆነም በሚገባ ተረድታለች። ይህ ሐሳብም በነቢዩ ኤልያስ የገድል ጽሑፍ ውስጥ በግልጽ በ (Ethiopian Manuscript Microfilm Library, 6903) ሰፍሮ እናገኘዋለን። ይህንን የምድር ጭንቀት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብም[13] የተለያዩ ምሁራን በተለያየ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ለማብራራት ሞክረዋል።

> ግዕዝ፡ ወፈርሀት፡ ምድር፡ ወርዕደት፡ እምነ፡ ቃሉ፡ ወትቤ፡ ምድር፡ በቅድመ፡ ኤልያስ፡ ነቢይ፡ ሐዘን፡ ዐቢይ፡ ወረደ፡ ላዕሌየ፡ ፡ አሌ፡ ልየ፡ ወለእለ፡ ይነብሩ፡ ላዕሌየ። አሌ፡ ልየ[14] ፡ ለዝ፡ ብእሲ፡ ጽኑ [0] ሐዘን፡ አልቦ፡ ዘየኀሥሦ፡ ወዘይስእሎ፡ አነ፡ አአምሮ፡ ለአምላኪየ፡ ኤሎሄ፡ ፈጣሪየ፡ መሐሪ፡ ውእቱ፡ ወበከመ፡ ብዝኀ፡ መዓቱ፡ ብዙኅ፡ ምሕረቱ፡ ላዕሌየ (EMML-6903 T159vb- T159ra) ።

> አማርኛ፡- ከቃሉ የተነሣ ምድርም ፈራች፤ እንዲሁም ተንቀጠቀጠች። በነቢዩ ኤልያስ ፊትም ምድር እንዲህ አለች፣ ታላቅ ሐዘን በእኔ ላይ ወረደ፤ በእኔ ላይ ለሚኖሩትና ለእኔም ወዮልን አለች። ሐዘኑ ለበረታ ለዚህ ሰውም ወዮልኝ አለች፤ እሱን የሚለምነው እንዲሁም የሚፈልገው አይኖርም። እኔ ግን ፈጣሪየንና አምላኬን ዐውቀዋለሁ ይቅር ባይ ነው፤ እንደመዐቱ ብዛትም ምሕረቱ በእኔ ላይ እንዲሁ የበዛ ነው አለች።

ምድር ያለፈውን ቅጣት ስታስታውስ (ምልሰት)

ምድር፣ በዚህ የግዕዝ ጽሑፍ ክፍል ውስጥ የጥንት ታሪኳን እያነሣች ስትተርክና ከጥንቱ ፍጡር አዳም ጀምሮ እስከ ሎጥ ድረስ የገጠማትን ውጣ ውረድ በማስታወስ ለታዳሚዋ ስታስረዳ ትታያለች። ለዚህ አጽንኦት መስጫ መጽሐፍ ቅዱሳዊ

12 አምላኩን የረሳና ለሆዱ ያደረ ወይም አላማ የሌለው ሰው ሲሆን እንደ ምድር ግን ውክልና መስጠት ግዴታ አይደለም፣

13 Olley (1998:40) "When Elijah first burst onto the scene he described himself as one who stood before YHWH (17:1). Now he is invited to do just that (v.11) and he delays. It is only after the wind, earthquake, fire and sheer silence (v.12, NRSV) that Elijah went out and stood. Unexpectedly he simply repeats the same words as before. YHWH's presence has no made difference." Really this Olley's paragraph tells us the worries of the Earth with Earthquake.

14 (ሎቱ) የሚል ማስተካከያ ያስቀመጡ አንባቢዎች እንደነበሩ ተመልክቻለሁ፡፡ ፍጹም ስሕተት ነው፡፡ ሐዘኑ ለፀና ለዚህ ሰው እኔ ወዮልኝ አለች እንጂ (መሬት) ሐዘኑ ለፀና ለዚህ ሰው እሱ ወዮለት ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በምድር ጭንቀት ውስጥ የምናየው የግል ችግሯን እንጂ የምትጨነቅ ስለ ኤልያስ አዝናለት አይደለም፡፡ ሙሉ ሐሳቡም ይህንን አያስረዳም፡፡

ቃሉን ከዘፍጥረት 1፥1 ፣ 7፡ 4 ድረስ መመልከት ተገቢ ነው።

ምድር፡- ከአዳም ኀጢአት ጀምሮ እስከ ኖኅ ሕዝብ እንዲሁም በሰዶምና በገሞራ ምክንያት የደረሰባትን ቅጣት ታስረዳለች። እንዲህም አለች በኖኅ ሕዝብ ጥፋት ምክንያት ጎርፍ ተጥለቅልቆ አሰቃየኝ፤ እንዲሁም በሰዶምና በገሞራ ሕዝብ ጥፋት ምክንያት ደግሞ እሳት ዘነበብኝ፤ ሥቃይም ደረሰብኝ። በሌላ አገላለጽ ምድር ምን ያህል ተጨንቃ[15] እንደ ነበር መግለጧን የሚያሳይ ነው። ምንም እንኳን ባለፉት ብዙ ኀጢአቶች ምክንያት ከፈጣሪ ቅጣት ቢደርስባትም ቅሉ አሁንም በኤልያስ ዘመን በተመሳሳይ ሁኔታ ፈተናዎች ወይም መከራ ገጥሟታል። ነገር ግን ይህ ሁሉ መከራ ተደጋግሞ ቢደርስባትም፣ ኤልያስም አስቀድሜ ነግሬሽ ነበር እያለ ፊቱን ቢዞርባትም በመጨረሻ ግን ከፈጣሪዋ ምሕረት እንደምታገኝ ተስፋን ሰንቃለች። በብዙ ፍርሃትም ወድቃለች። የግዕዙ ገድለ ኤልያስም ከ (Ethiopian Manuscript Microfilm Library, 6903) ተወስዶ እንደሚከተለው ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሟል።

ግዕዝ፡ ወበቀዳሚ፡ መዋዕል፡ ሐዘነ፡ ላዕለ፡ ገብሩ፡ አዳም። ወበእንቲኣሁ፡ ተረገምኩ፡ ወድኅሬሁ፡ መሐረኒ፡ ወሰረየ፡ ሊተ፡ መርገምየ። ወካ ዕበ፡ ሐዘነ፡ ላዕለ፡ ሕዝበ፡ ኖኅ። ወአውረደ፡ ማየ፡ አይኅ፡ ወአጥፍኦሙ፡ ወካዕበ፡ ገብአ፡ ወመሐሮ፡ ለኖኅ፡ ወአድኅኖ፡ እምአይኅ። ወካዕበ፡ ሐዘነ፡ ላዕለ፡ ምድረ፡ ሰዶም፡ ወገሞራ፡ ወአጥፍኦሙ፡ ለኵሎሙ፡ እለ፡ የኀድሩ፡ ውስቴታ፡ በእንተ፡ እከየ፡ ምግባሮሙ። ወካዕበ፡ ገብአ፡ ላዕለ፡ ሎጥ፡ መሐሮ፡ ወአድኅኖ፡ እምነ፡ ሞት፡ ወካዕበ፡ ብዙኀ፡ ሰዐተ፡ እፈርህ (EMML-6903, T159ra - T159rb) ።

አማርኛ፡ ‘እንዲሁም በቀድሞው ዘመን በአዳም ባሪያው ላይ አዘነ፤ ስለእርሱም ተረገምሁ፤ በኋላም ይቅር አለኝ። እርግማኔንም ተወልኝ። ዳግመኛም በኖኅ ሕዝብ ላይ አዘነ፤ የጥፋት ውሃም አውርዶ አጠፋቸው። ዳግመኛም ተመልሶ ኖኅን ይቅር አለው። ከጥፋት ውሃም አዳነው። ዳግመኛም በሰዶምና በገሞራ ላይ አዘነ፤ ስለ ሥራቸው ክፋትም በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉንም አጠፋቸው። ዳግመኛም ወደ ሎጥ ተመልሶ ይቅር አለው ከሞትም አዳነው። እንዲሁም እኔ በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ እፈራለሁ› አለች ምድር።

የምድር በእግዚአብሔር ምሕረት አጽንኦት መስጠት

እናት ምድር[16] የተስፋ ምኞቷንና የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲሁም ከመከራ የምትወጣበት መንገድ እንደሚኖር በማጤን ሐሳቧን መግለጥ ትጀምራለች። በእርግጥ እርሷ የእግዚአብሔርን ምሕረት በመጠባበቅ ትማጸናለች፤ እንዲሁም ስለ ፍጡራን ሁሉ ትለምናለች። ይህ ሐሳብም እንደሌሎች ነቢያት እንዲሁም ልክ እንደ አሞጽ[17] ስለ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ምሕረትን እንደለመነው ዐይነት ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ አብርሃም እግዚአብሔርን ስለሰዶምና ገሞራ ሕዝብ ከመቅሠፍት እንዲተርፉ በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት 18 የጠየቀውን የምሕረት ምልጃም ያሳያል።

ቀጥሎ በሚመጣው የግዕዝ ጽሑፍም ምድር የእግዚአብሔርን ቸርነት በእርግጠኝነት ስትናገር ትታያላች። በእርሷና በእርሷ ላይ ለሚኖሩት ሁሉ ለሚመጣው መከራ ግን በምክንያተ ኤልያስ በጣም በሐዘን እርር ስትል ትታያለች።

ግዕዝ፡- ወአአምር፡ ከመ፡ እግዚእየ፡ መሓሪ፡ ወይምሕር፡ ለእለ፡ ይነብሩ፡ ላዕሌየ፡ ወበእንተ፡ ጻድቃን፡ ይምሕር፡ ኃጥኣነ፡ ፡ ወአነ፡ ዐቢይ፡ ሐዘን፡ ብየ፡ እምነ፡ ኤልያስ፡ ነቢይ። በሐዘን፡ ጸውዐ፡ በዐቢይ፡ ቃል፡ ወአንቀልቀለ፡ መሠረታትየ፡ በታሕቱ፡ ወግብረ፡ እደዊሁ፡ ዲበ፡ ባሕር፡ ወሥልጣኑ፡ ዲበ፡ የብስ። ወዐርገ፡ መዐቱ፡ ከመ፡ ድምፀ፡ አንበሳ፡ ነጐርጓሩ፡ ወይፈርሁ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ፡ ወአንቃዕደወ፡ ወርእየ፡ ደመናተ፡ ወፈርሀ፡ ደመናት፡ ወተመይጡ፡ በሰማይ (EMML-6903, T159ra - T159rb) ።

አማርኛ፡- እኔም ጌታየ ይቅር ባይ እንደሆና በእኔ ላይ የሚኖሩትንም ሁሉ ይቅር እንደሚል አውቃለሁ። ስለጻድቃን ብሎም

15 1 Kings 18:1. “Now after a long time, the word of the Lord came to Elijah, in the third year, saying, Go and let Ahab see you, so that I may send rain on the earth.”

16 This is a literary name of the Earth. Mother Earth is imaged as human being to ask mercy from the Prophet.

17 The prophet Amos for instance implores God’s mercy affirming that the people is weak and cannot survive without God’s forgiveness (Amos 7:1-6).

> ጎጥአንን ይቅር ይላልና። እኔም ከነቢዩ ኤልያስ የተነሣ ታላቅ ሐዘን አድሮብኛል አለች ምድር። ኤልያስም በታላቅ ቃልም በሐዘን አጉረመረመ፤ መሠረቴም ከሥሩ ተነዋወጠ (መሠረቶቼም ከታች ተናወጡ)። የእጁ ሥራ በባሕር፣ ሥልጣኑም በየብስ ላይ ወደ ሚኖር መዓቱም ዐረገ። ጉርምርምታውም እንደ አንበሳ ድምጽ ነው። ከዚህ የተነሣ ሕዝቡም ሁሉ ይፈሩ ጀመር። እርሱም ወደላይ እንጋጦ ደመናትን ተመለከተ፤ ደመናትም ፈርተው በሰማይ ተመለሱ፤ ትላለች ምድር።

በሚገርም ሁኔታ እንደዚህ የረዘመ የግዑዝ አካል ረጂም ንግግር በሃይማኖት መዛግብት ምናልባትም ከጥቂቶች አንዱ ሊሆን ይችላል ወይም ላይኖር ይችላል።ይህም የአጥኚው ብቸኛው ትዝብት ነው።

የምድር ተቃውሞ በንጉሥ አክአብ ላይ

እናት ምድር፣ በንጉሥ አክአብና በሚስቱ ጣኦት አምላኪነት እንዲሁም በእግዚአብሔር ፈንታ በኣል ለተሰኘ ጣኦት በመስገድ በእርሷ ላይ ላመጡባት መከራ አክአብን በምክንያትነት ትወቅሳለች። በእርግጥ አክአብና ኤልዛቤል ነቢያተ ሐሰትን እንደ ካህናት ሾመው ሲበድሉ እንዲሁም የምስኪኑን ናቡቴን የወይኑን መሬት በግፍና በሐሰት ቀምተው እንዳስገደሉት ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል። እኛ በኣል ለተሰኘ ጣኦትም አምላኪዎች ነን ወይም አምላካችን ነው ብለውም ተቀብለውት ነበር።

ምድርም ልክ በዘፍጥረት አስራ ስምንት እንደተጠቀሰው እንደ አብርሃም ሐሳብ በተመሳሳይ ይዘት እግዚአብሔርን እንዲህ በማለት ትማጸነዋለች፤ እንዴት ስለኀጥኣን ብለህ ጻድቃንን ወይም ንጹሓንን ጭምር በጅምላ ታጠፋለህ። በእርግጥ ምድር ይህንን ስትናገር ነቢዩ ኤልያስ ከእግዚአብሔር ጎን መቆሙን በደንብ የተገነዘበች ይመስላል። በሌላ አገላለጽ እግዚአብሔር ኤልያስ ሰምቶ አጸፋ እንደሚሰጥ መገንዘቧን ያሳያል። እንደአንድ ግለሰብም ጉዳዩን ወደ እግዚአብሔር እንደሚያደርስ ነገሩን ተሸክሞ ሄዶ አቤቱታ ማቅረቡን ምድር ተረድታለች። በእርግጥ የዚህ ገድል ሐሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያፈነገጠ ባይሆንም ቅሉ ምድር ግን የሰው ባሕርይን በግልጽ ተላብሳ የምትታይበት ክፍል ይህ ነው (Ethiopian Manuscript Microfilm Library, 6903)

በሚቀጥለው የግዕዝ ጽሑፍ የምድርን ሰውኛ ገጸ ባሕርይ መላበስን በደንብ ማጤን ያስችላል።

> ግዕዝ፡- ወካዕበ፡ ትቤሎ፡ ምድር፡ ዝንቱ፡ ኵሉ፡ ሐዘን፡ ዘረከበኒ፡ በአከአብ፡ ንጉሥ፡ እፎ፡ እትናገር፡ በእንቲኣየ፡ ጎበ፡ ኤልያስ፡ ነቢይ፡ ወትቤሎ፡ በእንተ፡ ኃጥኣን፡ ወረሲዓን፡ ታጠፍእ፡ ጻድቃነ፡ ወንጹሓነ። አነ፡ አአምር፡ እግዚእከ፡ ዘወሀበከ፡ ሥልጣነ፡ ወኢያእመሮ፡ አከአብ፡ ንጉሥ፡ ለአማልክቲ፡ ወለጣዖቲ፡ ከመ፡ አልቦሙ፡ ኀይል (EMML-6903, T159ra - T159rb)።
>
> አማርኛ፡ ዳግመኛም ምድር እንዲህ አለችው፤ ይህ ሁሉ ሐዘን የደረሰብኝ በንጉሥ አክአብ ምክንያት ነው። በነቢዩ ኤልያስ ዘንድስ እንዴት እናገራለሁ አለች፤ ዳግመኛም ስለበደለኞችና ስለ ኀጢአተኞችስ ጻድቃንንና ንጹሐንን ታጠፋለህን አለችው። በእርግጥ እኔም ጌታህ ለአንተ የሰጠኽን ሥልጣን አውቃለሁ። ንጉሥ አክአብም አማልክቱንና ጣዖታቱን ኀይል እንደሌላቸው አወቃቸው።

ምንም እንኳን አክአብ ለፈጣሪው ባይመችምና ለምድር መሠቃየት ምክንያት ቢሆንም ቅሉ በመጨረሻ ግን ጣኦታቱና አማልክቱ ኃይላቸው ደካማ እንደሆነ የተገነዘበ ይመስላል። ይሁንም እንጂ ከአክአብ ትክሻ የወረደች ባይመስልም ጎን ለጎን ግን ከኤልያስ ጋርም መደራደሩን ፈልጋዋለች።

ለነቢዩ ኤልያስ የቀረበ የእናት ምድር ልመና

በእርግጥ እዚህ ላይ የግዕዙን ሐሳብ ስንመለከት በነቢዩ ኤልያስና በእግዚአብሔር መካከል ልዩነት ያለ ያስመስላል። ነገር ግን ምድር ኤልያስን የምትለምንበት ምክንያት የእግዚአብሔርን አምላክነት ችላ ብላ አይደለም። ይልቁንም ኤልያስን መያዝ እግዚአብሔርን መያዝ እንደሆነ ስለተገነዘበች ይመስላል። እዚህ ላይ ነቢዩ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ነገሮችን ማከናወን ይችል ይሆንን? የእግዚአብሔርን ፈቃድስ ነቢዩ ችላ ሊል ይችላልን ... ወዘተርፈ የሚሉ ሐሳቦች ቢነሡ እንኳን ሚዛን ሚደፉ አይሆኑም። ይሁንም እንጂ ምድር እንደ ፈጣሪ ሁሉ ኤልያስም ምሕረትን ያደርግላት ዘንድ ትማልዳለች። በምሕረት ዐይን እንዲዐያትም ትለማመጠዋለች (Ethiopian Manuscript Microfilm Library, 6903)።

ይህንን ሐሳብም በግልጽ ለመረዳት የግዕዙን አንቀጽ እንመልከት

> *ግዕዝ፡ ወካዕበ፡ ትቤሎ፡ ምድር፡ ለእመ፡ ትገብር፡ ፍትሐ፡ ለማእሰርከ፡ ዘአሰርከ፡ ወትከውን፡ መሐሬ፡ ከመ፡ አምላክከ፡ ወይሴባሕ፡ እግዚእነ፡ በተግባሩ፡ ወይትኀፈሩ፡ አማልክት፡ ወእለ፡ ያመልክዎሙ፡ ወእምድኅረ ዝ፡ ነገር፡ ካዕበ፡ ተናገረት፡ ምድር፡ ወጸውዐቶ፡ ለኤልያስ፡ ነቢይ፡ ወአስተምሐረት፡ ሎቱ፡ ወትቤሎ፡ አነ፡ አኀሥሥ፡ እምኔከ፡ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ትምሐረኒ፡ ወከመ፡ ትምሐር፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ላዕሌየ* (EMML-6903, T159ra - T159rb) ።
>
> *አማርኛ፡- ዳግመኛም ምድር እንዲህ አለችው፣ ያሠርኸውን እሥራት የተፈታ ብታደርገውስ እንደአምላክህ ይቅር ባይ ትሆናለህ ወይም ይቅር ባይ ትባላለህ። በዚህም ምክንያት ጌታችንም በሥራው ይመሰገናል። እንዲሁም አማልክትና የሚያመልኳቸውም ያፍራሉ። ከዚህም በኋላ በድጋሜ ምድር ተናገረች፣ ነቢዩ ኤልያስንም እንዲህ ስትል ጠራችው፣ ተማፀነችወም፤ የእግዚአብሔር ነቢይ ሆይ በእኔ ላይ የሚኖሩትንና እኔንም ይቅር ትለኝ ዘንድ ከአንተ ምሕረትን እፈልጋለሁ አለችው።*

ከላይ ስንመለከታቸው የነበሩ ሐሳቦች ሁሉ የምድርን ጭንቀት፣ የምድን ረጅም ንግግር የነቢዩ ኤልያስን አቋም፣ **የነቢዩ ኤልያስን ቀናኢነትንና የምድርን ጥብቅ ልመናን ለማስዳሰስ ተሞክሯል።**

የነቢዩ ኤልያስ አስደንጋጭና አሳዛኝ ምላሽ ለምድር

በዚህኛው የትንታኔ ክፍል ውስጥ ሁለት ነገሮችን እንመለከታለን። አንደኛው ነቢዩ ኤልያስ በጣም ተናዶና አዝኖ ጩኸት በማሰማት ምድርን ሊለያት ሲሞክር እንመለከታለን። በሌላ በኩል ደግሞ ኤልያስ ለምድር ምንም ዐይነት የሐሳብ ለውጥ እንደማያደርግና በእግዚአብሔረር ውሳኔ ቅጣት እንደሚያስተላልፍባት ይናገራል። ቅጣቱም ተግባራዊ እንደሚደረግና ንጉሥ አክአብ የአማልክቱን አፍቅሮት ወይም አምልኮት እስኪተው ድረስ ሰማይ ዝናምን እንዳይሰጥ[18] ፣ ምድርም የዘሩባትን እንዳታበቅል፣ አዝእርትም ፍሬ እንዳይሰጡ እስከማድረስ የሚተገበር ይመስላል። ነቢዩ ኤልያስም ከምሬት በሚመስል ቃል ምድርን ለአንድ ጊዜ ብቻ የምክር ወይም የማስጠንቀቂያ ቃል ሳይሰጣት እንዳልቀረና ደጋግሞም እንደነገራት፤ እሷም ሰምታ ችላ ያለችው በሚመስል ቃል እኔ ብዙ ጊዜ ለፍልፌያለሁ አንቺ አልሰማኝ አልሽ እንጂ የሚል ይመስላል፤ እንድታስታውስም ሲነግራት ይታያል። በእስራኤል አምላክ በመማልም ውስኔውን እንደማይቀይር ያስረዳታል። በዚህ ሐሳብም የምድርንና የኤልያስን አለመግባባት እንዱሁም የጠነከረ ቅራኔ በመካከላቸው መፈጠሩን በገድሉ ውስጥ በደንብ እንመለከታለን (Ethiopian Manuscript Microfilm Library, 6903)።

ይህንን ሐሳብ የሚያጠናክረው የግዕዝ ሥነ ጽሑፍም ከታች እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> *ግዕዝ፡- በሐዘን፡ ጸንዐ፡ ኤልያስ፡ ነቢይ፡ ወይቤላ፡ ለምድር፡ አነ፡ ነገርኩኪ፡ ቀዲሙ፡ ብዙኀ፡ ጊዜ፡ ወአኮ፡ አሐተ፡* **ዕለተ፡ ወይእዜኒ፡** *ዘመሐልኩ፡ በሕይወተ፡ እግዚእየ፡ ወአምላኪየ፡ ቀዲሙ ኢይሔሱ፡ ወኢያወርድ፡ አውሉ፡ ወዝናመ፡ ላዕለ፡ ምድር፡ ቤተ፡ አክአብ፡ ንጉሥ ። ወእከልእ፡ እምኔሆሙ፡ ዘመነ፡ መዋዕል፡ እስከ፡ የአምሩ፡ ኀይለ፡ አማልክቲሆሙ፡ ወአነ፡ ኣአምር፡ ኀይለ፡ አምላኪየ* (EMML-6903, T159rb - T160va) ።
>
> *አማርኛ፡- ነቢዩ ኤልያስም ሐዘኑ በጣም በረታ። ምድርንም እንዲህ ሲል ተናገራት፤ "እኔ አንድ ቀን ብቻ አይደለም፤ ብዙ ጊዜ አስቀድሜ ነግሬሻለሁ አላት። ዛሬ ግን በአምላኬና በጌታየ ሕይወት አስቀድሜ የማልሁ በመሆኔ አልዋስም፤ በንጉሥ አክአብ ቤትና በምድር ላይ ዝናምና ነፋስን አላወርድም። የአማልክቶቻቸውን ኀይልም እስከሚረዱ ድረስ ከእነእርሱ ለዓመታት ሁሉን እከለክላለሁ። እኔ ግን የአምላኬን ኀይል አውቃለሁና ! " ሲል ተናገረ።*

የክርክር ፍጻሜና የቅጣት ጅማሮ በምድር ላይ

18 According to the prayer of Elijah the Earth faced an absence of rain, 1Kings 17:1.

አንባቢ ከዚህ ቀጣይ የግዕዝ ጽሑፍ የሚረዳው ነገር ቢኖር የሁለቱን ውይይት ድምዳሜና የኤልያስን ብቸኝነት ወይም ያላወቀና ያልሰማ በመምሰል ሽሽት የመረጠበትን መንገድ ነው። እግዚአብሔርም ነቢዩ እንዳይራብበት የኦፍ ሞግዚት አዘጋጅቶለት በዚያው እንዳስቀመጠው ቀጣዩ ክታብ ያስረዳል። ከዚህ በመቀጠል ቅጣቱም ተፈጻሚ ተደረገ፤ የዝናም እጦት ተከሰተ፤ ድርቅ[19] ም በምድር ላይ ተዘረጋ፤ እንዲሁም በምድር ላይ የሚኖሩ ፍጡራን እንዲሞቱ ተፈረደባቸው።

በቀጣይ ክፍል የተቀመጠውን የግዕዝ ጽሑፍ እንመልከት፡

ግዕዝ፡- ዘንተ፡ ቃለ፡ ተናገራ፡ ኤልያስ፡ ነቢይ፡ ለምድር፡ ወሖረ፡ እምኔሃ፡ ወዐርገ፡ ደብረ፡ ዘይብልዎ፡ ኪሩብ[20] ፡ ማእከለ፡ እብን፡ ዐቢይ፡ በኣት፡ ወቦአ፡ ከመ፡ ዘኢያእመረ፡ ዘአውረደ፡ መቅሠፍተ፡ ላዕለ፡ ምድር፡ ወእግዚአብሔር፡ ገብረ፡ ሎቱ፡ ወሲሳዮ፡ ይፌኑ፡ ሎቱ፡ ምስለ፡ ዖፍ፡ ወማየኒ፡ ዘይሰቲ፡ እምነ፡ ዐይነ፡ ሙሓዘ፡ ፈለግ፡ ወኮነ፡ ቀዳሚ፡ ዓመት፡ ወበዓመት፡ የብሰ፡ ማየ፡ ባሕር፡ ወጠፍአ፡ ኵሉ፡ ዘሀሎ፡ ውስተ፡ ምድር፡ በጽምእ። ወተዘርዘረት፡ ምድር፡ ወኵሉ፡ ዘላዕሌሃ (EMML-6903, T159rb - T160va) ።

አማርኛ፡ ነቢዩ ኤልያስም ለምድር ይህንን ቃል ተናግሯት ከእርሷ ሔደ፤ በታላቅ ድንጋይ መካከል ወደሚገኝ ቦታ ኪሩብ ወደ ሚባል ተራራም ወጣ። በምድር ላይ ያወረደውን መቅሠፍትም እንዳለወቀ ሆኖ ወደ ቦታው ገባ። እግዚአብሔርም ምግቡን ከዖፍ ጋር ይልክለት ዘንድ አደረገለት። የሚጠጣውንም ከምንጭ ዐይን ከሚፈሰው ወሃ አደረገለት፤ አንድ ዓመትም ሆነው፣ ሁለትና ሦስት ዓመትም ሆነው።የባሕሩ ውሃም ደረቀ፤ በውሃ ጥምም በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ ጠፋ፡ ፡ ምድርም ተበታተነች፤ በላዩዋ ላይ ያሉትም ሁሉ እንዲሁ ተበታተኑ።

የሕይወት መጥፋትና የምድር ውድመት

ቀጥሎ በምንመለከተው የግዕዝ ጽሑፍ ምድር ሠቀቀን ውስጥ ገብታለች፤ ቅጣቱም ተግባራዊ ተደርጓል። ዕጽዋት፣ እንስሳት፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉ ንጹሓንን ጨምሮ በመቅሠፍት ተመትተዋል። 1ኛ ነገ ምዕራፍ 17 ጀምረህ ተመልከት።

ቀጣዩ የገድሉ ግዕዝ ጽሑፍ፡-

ግዕዝ፡- ወዝንቱ፡ ኵሉ፡ ኮነ፡ በኀይለ፡ ጽንዑ፡ ለኤልያስ፡ ነቢይ፡ ወበጠለ፡ ዝናመ፡ ክረምት፡ ዘርእ፡ ወማእረር፡ ወኀደገ፡ ነፋስ፡ ወደመና፡ ወተመርዐት፡ ምድር፡ ወኵሉ፡ ዘላዕሌሃ፡ ማሰነ፡ ወጠፍአ፡ ድምፆሙ፡ ወየብሰ፡ ወይን፡ ወኵሉ፡ ፍሥሓሆሙ፡ ለሰብእ፡ ጠፍአ፡ በምድር፡ ወጠፍኡ፡ መኃትው፡ ወሞቱ፡ ነገሥት፡ በረኃብ፡ ወበጠለ፡ ብዕሎሙ፡ ለብዑላን፡ ወበጠለ፡ ሥልጣኖሙ፡ ወትእቢቶሙ፡ እደዊሆሙ፡ ለሲኦል፡ ወሞቱ፡ ሕፃናት፡ ወተቀብሩ፡ ሠናያን፡ ዕደው (EMML-6903, T160va- T160vb) ።

አማርኛ፡ ይህ ሁሉ ነገርም በነቢዩ ኤልያስ የጥንካሬው ኀይል ተደረገ። የክረምት ዝናም እንዲሁም ዘርእና መከርም ጠፋ፡ ፡ ነፋስና ደመናም ተቋረጡ። ምድርም ተኮነነች፤ በላዩዋ ላይ የሚገኙትም ሁሉ እንዲሁ ሆኑ። ድምጻቸውም ፈጽሞ ጠፋ። ወይንም ደረቀ፤ የሰዎች ሁሉ ደስታቸውም በምድር ላይ ጠፋ። መብራቶችም ጠፉ፤ ነገሥታትም በረኀብ ሞቱ፡ ፡ የባለጸጎች ሀብታቸውም ጠፋ፤ ሥልጣናቸውና ትዕቢታቸውም ጠወለገ፤ ጎልማሶቻቸውም ለሲኦል ተዳረጉ፤ ሕፃናትም ሞቱ፤ ውበታቸው ያመረ ወጣቶችም ተቀበሩ።

---

19 Ps. 46:7-8 "The nations were angry, the kingdoms were moved; at the sound of his voice the earth became like wax", I kings 19:11-13 "Then the Lord went by, and mountains were parted by the force of a great wind, and rocks were broken before the Lord; but the Lord was not in the wind. And after the wind there was an earth-shock, but the Lord was not in the earth-shock. And after the earth-shock a fire, but the Lord was not in the fire. And after the fire was the sound of a soft breath. And Elijah, hearing it, went out, covering his face with his robe, and took his place in the opening of the hole".

20 This is an amazing word appeared only in the five hagiographies. But in other texts narrations including bible the common name is Koreb (**ኮሬብ**). This is really for Ethiopian writing and explaining style.

ይህ ሁሉ መቅሠፍት የተከናወነውም የምድርና የኤልያስ ድርድር እንዲሁም ውይይት ከተቋጨና ያለስምምነት ከተበተነ በኋላ ነው።

ከምድር የራቀው የሐሤት እጦት

በደረሰው አስከፊ መቅሠፍት ምክንያት ምድርና በምድር ያሉ ሁሉ ጭንቅ ውስጥ ገብተዋል። ነቢዩ ኤልያስም በፈጣረው ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ አስከፊው መቅሠፍትም በእንስሳትና በዕጸዋት ላይ ብቻ ሳይገደብ ለሕፃናት ጭምር አሠቃቂ ሆኗል። ነቢዩ ኤልያስ ግን ይህ ሁሉ ነገር እየተከናወነ ለኦፉም ምስጋና ይግባውና በልቶና ጠጥቶ ይኖር ነበር። በእሱ ላይ ምንም ዐይነት ተጽእኖ እስካልደረሰበት ድረስ እሱም በምድር ላይ የደረሰውን ችግር የረሳ መስሏል። የግዕዙን ንባብ እንመልከት፡-

ግዕዝ፡ ወኢይሰማዕ፡ ቃለ፡ ከብካብ፡ ወኢኀልቀታት፡ ውስተ፡ እደዊሆሙ፡ ወጠፍአ፡ ወርቅ፡ እምድር፡ ወፍሥሐ፡ እምሕዝብ። ወበጠለ፡ ትፍሥሕቶሙ፡ ለደናግል፡ ወለዕደው፡ ሠናያን፡ ወየብሰ፡ አፉሆሙ፡ ለሕፃናት፡ እለ፡ ይጠብዉ፡ ወኢተረከበ፡ ሐሊብ፡ እምእሞሙ፡ ፡ ወሞቱ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ወእንስሳ፡ ወአራዊተ፡ ገዳም፡ በዘኢተረከበ፡ ዘይበልዑ። ወተመርዐት፡ ምድር፡ በቃለ፡ ኤልያስ፡ ነቢይ፡ ወእግዚአብሔር፡ ሰምዐ፡ ስእለቶ፡ ወአዕበዮ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ፍጥረቱ፡ ወዘንተ፡ ዘገብረ፡ እግዚእነ፡ መሲሕ፡ ዘይሰሪ፡ ለነ፡ ኀጢአተነ፡ ወይገብር፡ ሰላመ፡ ለኵሉ፡ ፍጥረት (EMML-6903, T160va- T160vb) ።

አማርኛ፡ የሠርግ ድምጽም አይሰማም፤ በእጆቻቸውም ቀለበቶች የሉም፤ ወርቅም ከምድር ጠፍቷል። ከሕዝብም ደሰታ ጠፍቷል፤ የቆነጆዎች ኀልማሶችና ልጃገረዶች ደስታቸውም ተቆርጧል። የሚጠቡ ሕፃናትም አፋቸው ደርቋል፤ የናቶቻቸው ጡት ወተት የለውምና፤ የሰማይ ወፎች፣ እንስሳትና የዱር አውሬዎችም የሚመገቡት የላቸውምና ሞቱ። ምድርም በነቢዩ ኤልያስ ቃል ተኮነነች፤ እግዚአብሔርም የነቢዩን ልመና ሰምቶ ከፍጥረቱ ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አደረገው። ይህንን ያደረገና ኀጢአታችንን የሚያሥተሠርይ ቅቡዕ የሆነ ጌታችን ሰላምን ለፍጥረት ሁሉ ያደርጋል።

በዚህ የገድል ጽሑፍ ውስጥም በሰው ልጆች ላይ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ዕረፍት ያጣውን ኅሊና ሰብእና ሥቃይም መረዳት ይቻላል። የሥነ ጽሑፉ አንዱ ፋይዳም ይህንን ማሳየት ነውና።

የምድር ቅሬታና እንደገና ወደ ንግግር መመለስ

ምድር በተወረወረባት ቅጣት ምክንያት እንደገና ከነቢዩ ኤልያስ ምሕረትን ለመጠየቅ ወይም እንደገና ወደ ውይይቱ[21] ለመመለስ ተዘጋጅታለች። ኤልያስ ባደረሰባት ውጣ ውረድ ምክንያትም ከልብ አዝናለች። የደረሰባትን መከራ ሁሉ በአደባባይ ተናግራለች፤ የእናትነትን ባሕርይ ተላብሳም ምሕረትን ከኤልያስ እየፈለገች ትገኛለች። ለኤልያስም ጠንከር ያለ ጥያቄ የምታቀርብ ትመስላለች፡ ፡ ከምድር አልተፈጠርህምን፣ ስለኃጥኣንስ ጻድቃንን ማጥፋቱ ተገቢ ነውን፣ ከጡቴስ ወተትን አልተጎነጨህምን.. እያለች በጥያቄዎች ምታጣድፈው ትመስላለች (Ethiopian Manuscript Microfilm Library, 6903) ።

እንደገና ምድር ኤልያስን ታነጋግረውን የሚለውን ሐሳብ ለመረዳት እስቲ በሚቀጥለው ክፍል የገድሉን የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ እንመልከት።

ግዕዝ፡ (ወዝንቱ፡ ኵሉ፡ መቅሠፍት፡ ዘረከባ፡ ለምድር፡ ኢገብአ፡ ሐዘኑ፡ ለኤልያስ፡ ነቢይ፡ ወኢኀደገ፡ መዐቱ፡ ላዕለ፡ ሰብእ፡ ወኀሠሠቶ፡ ምድር፡ ለኤልያስ፡ ካዕበ፡ ወተደርዐት፡ ሎቱ ምድር፡ ወትቤሎ፡ አነ፡ እሴአለከ፡ ከመ፡ ትገብር፡ እም፡ ለውሉዳ፡ በዘትምሕር፡ ዘላዕሌየ፡ ኢመፍትው፡ ታጥፍእ፡ ጻድቃነ፡ በእንተ ኃጥኣን። ወካዕበ፡ ትቤሎ፡ ምድር፡ ለእመ፡ ኢሰማዕከኒ፡ ቃልየ፡ አንተ፡ ኢተፈጠርከኑ፡ እምሐመድ። ወለምንት፡ ትጸልኦሙ፡ ለእለ፡ ተፈጥሩ፡ በውስተ፡ ሐመድ፡ እፎ፡ ዘጠበውከ፡ ሐሊበ፡ እምኔየ፡ ለምንት፡ ትረስዐኒ፡ ኢነግድኑ፡ አንተ፡ ዘትነብር፡ ላዕሌየ፡ ኢገብርኑ፡ ወአበየ፡ ፈቲሐ) (EMML-6903, T160va- T160ra) ።

---

21 dialogue, the In addition to being a feature of fiction and drama which represents characters` speech, the dialogue is also a type of literature in which two or more people engage in a discussion. Among the earliest and greatest examples of the form are the Dialogues of Plato (fourth century B.C), which depict Socrates as the intellectual gadfly employing a question/ answer technique interlocutors. (Edward Quinn. 118: 2006. A dictionary of literature and thematic terms)

አማርኛ፡ ምድርን ይህ ሁሉ መቅሠፍት አግኝቷትም የነቢዩ ኤልያስ ሐዘን ግን እስካሁን ድረስ አልተመለሰም። በሰዎች ላይ የሚያወርደውን መዓትም አላቋረጠም፤ ዳግመኛም ምድር ኤልያስን ፈለገችው። ተገዛችለትና እንዲህም አለችው፣ በእኔ ላይ የሚኖሩትን ይቅር ትላቸው ዘንድ እናት ለልጆቿ እንደምታደርገው እማፀንሃለሁ። ስለ ኀጢአተኞችም እውነተኞችን ታጠፋ ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ዳግመኛም ምድር እንዲህ አለችው፤ አንተ ቃሌን ካልሰማኽስ ከአመድ አልተፈጠርህምን፣ ለምንስ በአመድ ውስጥ የተፈጠሩትን ትጠላቸዋለህ፣ እንዴት ከእኔ ወተትንስ ጠባህ፣ ለምንስ ትረሳኛለህ፣ በእኔ ላይ የምትቀመጥ ዐዲስ እንግዳስ ነህን፣ ፍርድን ያጓደለ አገልጋይስ ነህን አለችው።

በምድር ምክንያት መልአክ ለፈጣሪው ያቀረበው ጠንካራ ጥሪ

በዚህ ዐዲስ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ አንድ ገጸ ባሕርይ ብቅ ብሏል። እሱም የመላእክት አለቃ ሚካኤል[22] የተባለ መልአክ ነው። ይህ መልአክም ፈጣሪውን የሚያስቸግር ጥያቄም ያቀርባል። ይህ በሥነ ጽሑፉ ውስጥ ብቅ ያለው ንኡስ ገጸ ባሕርይ መልአክም ለጌታው ምድርና በእርሷ ላይ ያሉት ሁሉ ለምን ይጠፋሉ ብሎ ጠበቃ ሲቆም ያሳያል። ፈጣሪም ለነቢዩ[23] ታላቅ ሥልጣንን እንደሰጠው ይገልጽለታል። ለዚህ ሐሳብ አጽንኦት የሚሰጡ ምንጮችም Encyclopedia of religious and spiritual development / editors, Elizabeth M. Dowling, W. George Scarlett, (2006:355) እና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው።

የግዕዙን ጽሑፍ እንመልከት፡-

ግዕዝ፡- ወይቤሎ፡ ሚካኤል፡ ሊቀ፡ መላእክት፡ ለእግዚአብሔር፡ አኀሥሥ፡ እምኔከ፡ አምላኪየ፡ ለእመ፡ ኢኮነት፡ ዛቲ፡ ሰዐት፡ ተፍጻሜተ፡ ዓለም፡ በእንተ፡ ምንት፡ ዘጠፍአት፡ ምድር፡ ከመዝ። ወጠፍኡ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ላዕሌሃ፡ ወምንትኑ፡ ግብሩ፡ ለዝ፡ ብእሲ፡ አሐተ፡ ቃለ፡ ሶበ፡ አውፅአ፡ እምአፉሁ፡ ዝ አጥፍአ፡ ኵሎ፡ ዓለመ፡ ዘላዕሌሃ (EMML-6903, T160va- T160ra) ።

አማርኛ፡ የመላእክት አለቃ የሆነ ሚካኤልም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፤ "ይህቺ ጊዜ የዓለም መጨረሻ ካልሆነች አምላኬ ሆይ ከአንተ የምፈልገው ነገር አለ፤ ምድር እንደዚህ የጠፋች ስለምንድን ነው? በርሷ ላይ የሚኖሩትስ ሁሉ ለምን ጠፉ? የዚህ ሰው ሥራውስ ምንድን ነው? አንዲት ቃል ከአፉ ስላወጣ ብቻ ዓለምንና በእርሷ ላይ ያሉትን ሁሉ ያጠፋ ለምንድን ነው?" አለው።

ኤልያስ የቅጣት ዓላማውን ለማሳካት ያለው ቁርጠኝነትና የገጠመው ችግር

ምንም እንኳን ኤልያስን የምድር ጭንቀት ባይገባውና የሚያወርደውን መቅሠፍት እያራዘመ ቢቀጥልም ቅሉ ብድር በምድር ነውና ፈጣሪው እሱንም ፊት የነሣው ይመስላል፤ በኦፎች የሚመላለስለት ምግብም[24] ተቋርጧል። በሌላ በኩል እግዚአብሔር ለመሬት ያዳላ ይመስላል። በእርግጥ ምድርም በንግር መልክ የፈጣሪን ቸርነትና እንደሚምራትም አስቀድማ ትናገር ነበር። በፊት ለፊት የሚታየውን የገድሉን ሥነ ጽሑፍ እንመልከት፡-

22 Indeed, first time God ordered Elijah to evacuate to Horeb. However, the Angel was his director of the way and place. See I kings 19:5-8 "And stretching himself on the earth, he went to sleep under the broom-plant; but an angel, touching him, said to him, Get up and have some food. And looking up, he saw by his head a cake cooked on the stones and a bottle of water. So he took food and drink and went to sleep again. And the angel of the Lord came again a second time, and touching him said, Get up and you have some food, or the journey will be overmuch for your strength."

23 "Prophets did not always work alone; they often worked in groups. Some prophets had elaborate rituals, driving themselves into a frenzy dancing, singing, and playing instruments. Their goal was to come into a state where they could get closer to God. It is out of this group of prophets that the great prophet Elijah emerged. In the year 886 B.C.E., Elijah is called by God to prophesy his words to Israel. Elijah's voice rallied the political opinion of King Ahab who was Jewish but participated in both Jewish and pagan rituals. Ahab's pagan wife, a Phoenician princess, Queen Jezebel, performed public acts of paganism rather than Judaism. The two along with their followers and priests worshipped pagan deities of Baal and Ashara. Elijah soon found himself with an enemy, and his task was to keep King Ahab honest and faithful to God and the laws of Israel."(Encyclopedia of religious and spiritual development, 2006:355)

24 The Ethiopic commentary of praise of St. Mary "**ከዚህ በኋላ ፍጡር ጨካኝ ነውና ዝናም አዝንም ብሎ የማይለምነው ሆነ፡፡ ምግቡን ቋዓት አስቀሩበት ውሃውን ሊጠጣ ቢያይ ውሃው ደረቀበት፡፡ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ሑር ምድረ ስራፕታ ወበህየ ትሴስየከ ብእሲት መበለት ብሎታል፡፡ከዚህ በኋላ ስራፕታ ሄደ ወረከበ ብእሲተ መበለተ እንዘ ተዐጥብ ክልኤተ ዕፀወ እንዲል፡፡**" (1954: 97) In this context the idea of the Angel and this commentary text have shared the same thoughts. The Angel was begging the God to save the Earth and those who are dwelling on it.

ግዕዝ፡- ወነበረ፡ ኤልያስ፡ በመዐት፡ ወኢገብአ፡ ኀበ፡ ምሕረት፡ ወከልኦ፡ እግዚአብሔር፡ ለዖፍ፡ ይፌኑ፡ ለኤልያስ፡ ሲሳዮ። ወጸንሐ፡ ኤልያስ፡ ዕለተ፡ ወዕለተ፡ ወኢመጽአ፡ ዖፍ። ወይብል፡ ኤልያስ፡ በልቡ፡ ምንትኑ፡ ኢያምጽአ፡ ሲሳይየ፡ ኢረከበኑ፡ እንከ፡ ወሐረኑ፡ ያምጽእ፡ ወይኅሥሥ፡ ሲሳየ፡ ሊተ። ወኮነ፡ ዕለተ፡ ወኢመጽአ፡ ዖፍ (EMML-6903, T162vb- T162ra) ።

አማርኛ፡ ኤልያስም በመከራ ውስጥ ተቀመጠ፤ ወደ ይቅርታም አልተመለሰም። እግዚአብሔርም ለኤልያስ ምግቡን በኦፍ[25] አድርጎ ይልክለት የነበረውን ከለከለው።ኤልያስም አንድ ቀን ጠበቀ፤ ሁለተኛ ቀንም ጠበቀ ኦፋም አልመጣም። ኤልያስም በልቡ ምግቤን ያላመጣ ለምንድን ነው፣ አላገኘምን፣ ምግቤን ፈልጎ ያመጣልኝ ዘንድስ አልሔደምን አለ፣ ሦስት ቀንም ሆነው፤ ኦፋም አልመጣም።

የነቢዩ ኤልያስ ጉዞ፣ ጭንቀትና ረኀብ

ኤልያስን ምግብ ማጣቱ[26] ና የኦፋ መቅረት ፍርሃት ውስጥ ከትቶታል። ብርታት ይሆነው ዘንድም ድንገት ወደለመደው ምንጭ ሊጠጣ ቢሄድም እንደጠበቀው የሆነለት አይመስልም፤ አሁን ጭንቀትና ፍርሃት በተራው ቦታውን የቀየረ ይመስላል። ግዕዙን እንመልከት፡-

ግዕዝ፡ [ወኀለየ፡ በልቡ፡ ወይቤ፡] ዖፍኑ፡ እንከ፡ ረከቦ፡ ዘይኄይሎ፡ ወነሥአ፡ እምኔሁ፡ ሲሳየ፡ ወኮነ፡ ፬፡ ዕለተ፡ ወ፭፡ ዕለተ። ወኤልያስ፡ ነቢይ፡ ይጸንሕ፡ ምጽአቶ፡ ለዖፍ። ወእምድኅረ፡ ኮነ፡ ስደስተ፡ ዕለተ፡ ደንገጸ፡ ወፈርሀ፡ ወደክመ፡ በረኃብ፡ ወወረደ፡ ከመ፡ ዘወረደ፡ ቀዲሙ፡ ኀበ፡ ፈለገ፡ ዐይነ፡ ማይ ዘይሰቲ፡ እምኔሁ (EMML-6903, T162vb- T162ra) ።

አማርኛ፡- ኤልያስ በልቡም እንዲህ ሲል አሰበ፤ ኦፉን የሚቀማው አግኝቶት ይሆንን፣ ምግቡንም ወስዶበትስ ይሆንን አለ። ዐራት ቀንም ሆነው፤ እንዲሁም አምስት ቀንም ሆነው። ኤልያስም የኦፋን መምጣት ይጠባበቅ ነበር። ስድስት ቀን ከሆነው በኋላ ፈጽሞ ደነገጠ፤ ፈራ፤ በረኀብም ደከመ፤ ቀድሞ እንደወረደበት ወደ ምንጩ ውሃ ከእሱም ይጠጣ ዘንድ ወረደ[27] ።

የኤልያስን ውሃ ጥምን ጥያቄ ምድር ስትከለክል

በዚህ የግዕዝ አንቀጽ ውስጥ ሁለት ነገሮችን እንመለከታል። አንደኛው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበረችው ምድርን የንዴት ስሜት[28] ዕናያለን። ሁለተኛው ደግሞ ምድርን ሰቆቃ ውስጥ የከተታት ኤልያስ በተራው ጸዋውን ሲቀበል እንመለከታለን። በዚህ ምክንያትም ምድር ኤልያስን እድል አግኝታ እንደገና ስትቀጣው እንመለከታለን። የእናትነትን ባሕርይ የተላበሰችው ምድር ዛሬ ንዴቷን መቆጣጠር አቅቷታል። በቀጣዩ የግዕዝ አንቀጽ እንመልከት፡-

ግዕዝ፡- ወፈትሐት፡ ምድር፡ አፉሃ፡ ወውኅጠት፡ ውእተ፡ ማየ፡ በቅድሜሁ፡ ወጸውዐቶ፡ ምድር፡ ወትቤሎ፡ ለኤልያስ፡ አንተ፡ ወልድ፡ ለምንት፡ ትጸልእ፡ ወላዲተከ፡ ኢጠበውከኑ፡ ሐሊበ፡ እምኔየ፡ እፎኑ፡ ዘአይበስከኒ፡ ወተኀሥሥ፡ እምአንብዕየ፡ ትስተይ፡ ኢመሐርከኒ፡ አንተ፡ ወይእዜኒ፡ ሕያው፡ እግዚአብሔር፡ እግዚእየ፡ ወፈጣሪየ፡ ዘመሐልከ፡ ቦቱ፡ ወኢይሔሱ፡ ኢያሰትዮ፡ ለጽምእከ፡ ወፈትሐት፡ ምድር፡ አፉሃ፡ ወውኅጠት፡ ውእተ፡ ማየ (EMML-6903, T162vb- T162ra) ።

አማርኛ፡ ምድርም በፊቱ አፏን ከፍታ ያንን ውሃ ዋጠችው። ምድርም ኤልያስን ጠርታ "አንተ ልጅ ለምንስ ወደ እናትህ ትመጣለህ? ወተትንስ ከእኔ አልጠባህምን? ያደረቅኸኝንስ እንዴት ከዕንባዬ ትጠጣ ዘንድስ ትፈልጋለህ? አንተም ይቅርታን አላደረግኽልኝም። ዛሬ ግን ጌታየንና ፈጣሪየን የማልሁበትን ዘላለማዊው እግዚአብሔርን አልዋሽም፤ የውሃ ጥምህንም አላረካህም (አላጠጣህም)"

---

25 **በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ቁራ አሞራ እንደሆነ እንጂ ኦፍ አይልም፡፡ ይህም የገድሉ ብቸኛ መገለጫ ነው፡፡**

26 1kings 17:7-10 Now after a time the stream became dry, because there was no rain in the land. Then the word of the Lord came to him, saying, Up! go now to Zarephath, in Zidon, and make your living-place there; I have given orders to a widow woman there to see that you have food.

27 17:2-5 Then the word of the Lord came to him, saying, Go from here in the direction of the east, and keep yourself in a secret place by the stream Cherith, east of Jordan. The water of the stream will be your drink, and by my orders the ravens will give you food there.

28 This is indicating that the dry stream which was around Elijah that God ordered him to drink from it. And this stream has delegated the entire surface of Earth including dwellings on the Earth.

አለችው። ምድርም አፏን ከፍታ ይህንን ውሃ ዋጠች።

የኤልያስ ልመናና የእግዚብሔር መልስ

ኤልያስ አሁን ነገሮችን ሁሉ ተረድቶ ወደ ፈጣረው ሙሉ ጥያቄውን አቅርቧል፤ ፈጣሪውም ልመናውን ሰምቶ መፍትሔ ሰጥቶታል። (' ወበእንተ ዝ፡ ሰአሎ፡ ኤልያስ፡ ለእግዚአብሔር . . . . . ።') በማለት የግዕዙ አንቀጽ ያብራራል። የአማርኛውን ቅንጭብ አንቀጽ እንመለከት። < < ስለዚህም ኤልያስ እግዚአብሔርን ለመነው[29] ። እግዚአብሔርም አንዲት ባል የሌላት ሴት አዝዛለሁ፤ እርሷም ቃልህ እስከሚፈጸም ድረስ በዚያ ትመግብሃለችና ስራጵታ ወደ ምትባል ሀገር ሒድ አለው፤ በዚህ ጊዜም ወደ ስራጵታ ሔደ። እነሆ ዛሬ የሆነውን፣ ወደ ባልቴቷ ቤት እንደ ሔደና የማይጎድል ማእድን፣ የሚጠጣውን ውሃና ቂጣንም እንዳገኘ ሰሙ።

ማጠቃለያና አስተያየት

የነቢዩ ኤልያስ ገድል በግዕዝ ተጽፎ የተገኘ ሲሆን በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብንና የሙሴ ሕግን ተከትሎ የተተረከ ጽሑፍ ነው። በሌላ በኩል የነቢዩ ኤልያስን ቀናኢነትና አምልኮተ ጣኦትን የሚቃዎም መሆኑን ጽሑፉ አስረድቷል። በሥነጽሑፍ ዓለም ውስጥ ከሚታየው አንዱ ውይይት ወይም ክርክር እንዲሁም ንግግር በሌላ አባባል ቃለ ምልልስ የሚባለው ሲሆን፣ ይህ የገድል የግዕዝ ጽሑፍም ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር እናት ምድርንና ኤልያስን እሰጣ አገባ ውስጥ ሲከት አልፎ ተርፎም በግጭት ሂደት ነገራቸው ጡዘት ላይ ሲደርስ ለአንባቢና ለታዳሚ በግልጽ ቀርቧል። በገለጻው ሥልትም እናት ምድር አብረዋት እስከሚኖሩ ፍጡራን በቅጣት ስትሠቃይ የጥናቱ ገለጻ አሳይቷል። ጥናቱም የአሊጎሪዝምን እሣቤ ወይም የማይናገር ግዑዝ ነገርን በማናገር ለፈጠራ ጽሑፍ ማስተማሪያና ምሳሌ ሊሆን እንደሚችል በትንሹም ቢሆን አስገንዝቧል። ይህ የገድል ጽሑፍ ከሌሎች ገድላት የሚለይበት ርእሰ ነገርም በሕይወት ለሚኖር ነቢይ ርእሱ ገድል ተብሎ መጻፉ ድንቅ ያደርገዋል። በጽሑፉ ውስጥም የምድርን ሰዋዊ ባሕርይ ከረጅም ንግግርና ጭቅጭቅ ጋር፣ የኤልያስን ጨካኝነት ከቀናኢነት ጋር፣ የአምላክን ቸርነት ከትዕግስት ጋር፣ የመላኩን አስታራቂነት ከመሠረታዊ ጥያቄ ጋር መቀመጡ ነባራዊውን የሕይወት ውጣውረድ ግንዛቤ የሚሰጥ ልዩ ጽሑፍ መሆኑ በጥናቱ ውስጥ ለመግለጽ ተሞክሯል፡ ፡ በመሆኑም ጽሑፉ ግነት የተሞላበትና ምድርን አፍ አስወጥቶ ችግሯን ያናገረ መሆኑን ጸሐፊው ተገንዝቧል። ሌላው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ጉዳዮችም በጠንካራና በውብ አገላለጽ በገድሉ ውስጥ መንጸባረቃቸውን ጥናቱ አሳይቷል። ለምሳሌ የሰማይ ዝናም እንዳይሰጥ መለጎም፣ የድርቅ ብዛትና በፍጡራን ላይ የደረሰው አሠቃቂ ክስተት ከመጽሐፈ ነገሥት የተወሰደ ሐሳብ እንደሆነ በምንጭ ተደግፎ በጥናቱ ታትቷል። እንዲሁም የምድርን አፍ አውጥቶ ማናገርም በትንሹም ቢሆን የመዝሙረ ዳዊት እሣቤ እንዳለበት መገንዘብ አስችሏል። የዚህ ገድል የግዕዙ አንቀጽም ወደ አማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋ በአጥኚው ተተርጉሟል።

አስተያየት

አጥኚው የተወሰነበት የጥናት ክፍል በገለጻ ሥልት ተመርኩዞ የምድርንና የኤልያስን ቃለ ምልልስ ወይም ክርክር ያሳየ ነበር፡ ፡ በእርግጥ በእያንዳንዱ ጥቅስ ውስጥ ምናልባትም ክርክር ብቻ ላይከሠት ይችላል። ነገር ግን በጥቅሱ ውስጥ የሚታዩት ነጥቦች እንደመንደርደሪያ ከመሆናቸው ባሻገርም፡- የምድርን ሰው-መሰል ቅርጽ፣ (Allegorical interpretation) የኤልያስ የአቋም ጽናትና እንቢ ባይነት፣ የእውነቱን ዓለም ንድፍ ወዘተርፈ የሚያመላክቱ ጥቅሶች ናቸው። በሌላ በኩል ለተጨማሪ ሥራ የገድሉን ታሪካዊ ፋይዳና ሥነ ምግባራዊ አስተምህሮውን እንዲሁም ከሌሎች ገድላት የተለየበትን ቁም ነገር ማጥናት ተገቢ ነው። ሆኖም የሥነ ጽሑፍ ዘውጉ ለየት ያለ በመሆኑ ይህ ኢትዮጵያዊ የግዕዝ ገድል በበለጠ ቢጣና ሀገራዊ የሥነ ጽሑፍ ልዕልናን ሊጠቁም ይችላል።

29 In sense, Elijah was in great fear at that time, the stream dried, the food absented and the family of Ahab and Jezebel hate him. So, the only option is begging of God. And after, he was success with the prayer.

References

Amsalu Aklilu. 1976. *History of Ethiopian literature.* Addis Ababa, (Unpublished).

A.W. Pink .1997. The Book of the Life of Elijah. Chapel Library 2603 West Wright St. Pensacola, Florida 32505 USA

Bnf Gallica Ethiopien, Project Number 133, France. (the collection of Geʿez manuscripts)

David Frankfurter .1994. "The Cult of the Martyrs in Egypt before Constantine: The Evidence of the Coptic "Apocalypse of Elijah" Vigiliae Christianae, Mar., 1994, Vol. 48, No. 1 (Mar., 1994), pp. 25-47. Published by Brill

Edward, Q. 2006. *A Dictionary of Literature and Thematic Terms* /second edition. / New York NY 10001.

EMIPMM - Project Number. 00226. and Betäkhnät library (with no number)

EMML- Project Number. 6903 (the collection of Geʿez manuscripts)

EMML- Project Number. 2796. (the collection of Geʿez manuscripts)

Encyclopedia of religious and spiritual development.2006. Editors, Elizabeth M. Dowling, W. George Scarlett, Printed in the United States of America on acid-free paper, Sage Publications, Inc. 2455 Teller Road Encyclopaedia Americana Vol. 13: 679

Francesca Prome Teabarone. 2008. "The Image of Prophet Elijah in PS. Chrysostom the Greek Homilies" ARAM, 20 (2008) 111-124. doi: 10.2F1.4P3. B/AARROANME.20.0.2033124 University of Palermo

Getachew Haile. 2008. *Geʿez Bäqällalu. Kəlləisina Yätäsfafa* New York Printing.

John W. Olley.1998. "*YHWH and His Zealous Prophet: The Presentation of Elijah in 1 and 2 kings*" Journal for the study of Old Testament, Baptist Theological college of Western Australia, 20 Hayman Rd, Bentley, WA6102, Australia.

Kaplan, S. 1982. *The Monastic Holy Man and the Christianization of Ethiopia 1270-1468.* Hebrew University (Unpublished Doctoral Dissertation).

Kaplan, S. 2012. Hagiographies and the History of Medieval Ethiopia, in: Languages and cultures of Eastern Christianity: Ethiopian (The worlds of Eastern Christianity, 300- 1500), V4, pp. 371-388, London and New York: Routledge.

Kidanawald Kifle. 1948. Mashafa Sawasiw Wägiss Wäamäzgäabä Kalat Haddis. Addis Ababa: Artistic Printing.

Michael A. Knibb. 1985. "The Ethiopic Version of the Lives of the Prophets, II: Isaiah, Jeremiah, Haggai, Zechariah, Malachi, Elijah, Elisha, Nathan, Ahijah, and Joel" The School of Oriental and African Studies, University of London, Vol. 48, No. 1 (1985), pp. 16-41.

Taddesse Tamrat. 1970. "Hagiographies and the Reconstruction of Medieval Ethiopian History" in Journal of Ethiopian Study.

Tesfaye Gebre Mariam. 1997. A Structural Analysis of Gädlä Täklä Haymanot. African Languages and Cultures, Vol. 10, No. 2, pp. 181-198 Published by: Taylor & Francis,Ltd. Stable URL: http://www.jstor.org/stable/1771714

... Treasure House of Mysteries .2012. “Explorations of the Sacred Text through Poetry in the Syriac Tradition,” New York, Saint Vladimir’s Seminary

Vlad Bedros. 2022. “The Prophet Elijah in Moldavian Iconography, ca. 1480–1530: Liturgical and Devotional Contexts”. ANASTASIS- Research in Medieval Culture and Art Vol. IX, No. 1/May 2022 www.anastasis-review.ro Yalew Endaweqe. 1998. Basic Principles and Application of Research, Alpha Publisher.

Zewdie Gebreegziabher. 2023. “Textual Value of an Ethiopic Woman Hagiography: Gädlä St. Fəqərtä Krəstos”. http://ijssrr.com editor@ijssrr.com Volume 6, Issue 5 May, Pages: 798-812